## ለተጨማሪ የማሞቂያ እና የፍጆታ አገልግሎት ቅናሾች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ!

የሚገኘው እርዳታ የቤተሰብ ስፋት፣ የቤተሰብ ገቢ እና ባለፉት 12 ወራት የነበረው የኃይል አቅርቦት ወጪ ላይ የተመሰረተ ነው።

| የቤተሰብ ስፋት | ከፍተኛው ገቢ |
|---|---|
| 1 | $51,777 |
| 2 | $67,709 |
| 3 | $83,641 |
| 4 | $99,573 |
| 5 | $115,504 |
| 6 | $131,436 |

## ገንዘብ ይቆጥቡ እና ብርዱን ይከላከሉ!

ቀጠሮ ለማስያዝ ዛሬውኑ ይደውሉ፡-

**617-665-6234**

ኦንላይን ያመልክቱ፡-

**www.cambridgema.gov/HeatingHelp**

እንዴት ማመልከት ይቻላል በሚለው ዙሪያ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች ለማግኘት QR ኮዱን ስካን ያድርጉ

**Home Energy Assistance Program (HEAP)**
*በቀድሞው መጠሪያው*
*የFuel Assistance Program*

የCambridge ከተማ አስተዳደር
Department of Human Service Programs
51 Inman St. (ምድር ቤት ወለል)
Cambridge, MA 02139

# Home Energy Assistance Program (HEAP)

በያዝነው የክረምት ወቅት የCambridge እና Somerville ነዋሪዎችን ብርድ ለመከላከል እና ገንዘብ ለመቆጠብ እናግዛለን!

የቤት ባለቤቶች እና ተከራዮች ለማመልከት ብቁ ናቸው!

## ይህ ምንድን ነው?

የCambridge Home Energy Assistance Program (HEAP) ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች የክረምት ወቅት የማሞቂያ ሒሳቦቻቸውን እንዲከፍሉ የሚረዳ በፌደራል ገንዘብ የተደገፈ ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም Fuel Assistance Program በመባል ይጠራ ነበር።

## ብቁ የሚሆነው ማን ነው?

ለማሞቂያ የሚከፍል እና በገቢ መመሪያዎቹ ውስጥ የሚወድቅ ማንኛውም ቤተሰብ ወይም ግለሰብ። Cambridge እና Somerville ውስጥ የሚኖሩ ተከራዮች እና የቤት ባለቤቶች ማመልከት ይችላሉ። የማሞቂያ ሒሳቦች ኪራያቸው ውስጥ የሚካተትላቸው ተከራዮችም ማመልከት ይችላሉ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

ቤተሰቡ በየዓመቱ አዲስ ማመልከቻ መሙላት እና ማንነት፣ ገቢ እና ማሞቂያን የሚመለከቱ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት። አንድ ቤተሰብ ብቁ ሆኖ ከተገኘ የማሞቂያ ሒሳቦቹ ለHome Energy Assistance ገቢ ይደረጉ እና ሠራተኞቹ የማሞቂያ ክፍያውን በቀጥታ ለአገልግሎት አቅራቢው ይከፍላሉ። የአንድ ቤተሰብ ማመልከቻ በHome Energy Assistance ውድቅ ከተደረገ ቤተሰቡ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ይችላል።

## የፕሮግራሙ ቀናት ምንድን ናቸው?

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር ወር ጀምሮ ማመልከቻዎችን ማስገባት ይቻላል። ፕሮግራሙ እ.ኤ.አ ከኖቬምበር1 -ኤፕሪል 30 ድረስ የማሞቂያ ሒሳቦችን ለመክፈል ይረዳል። እ.ኤ.አ እስከ ኤፕሪል 30 ድረስ ማመልከት ይችላሉ።

## እንዴት ነው ማመልከት የምችለው?

ከዚህ በፊት ከፕሮግራሙ እርዳታ ካገኙ በድጋሚ እንዲያመለክቱ ማመልከቻ በፖስታ ተልኮልዎታል። የመጀመሪያ ጊዜ እና ተመላሽ አመልካቾች በ**www.cambridgema.gov/HeatingHelp** ላይም ኦንላይን ማመልከት ይችላሉ።

የመጀመሪያ ጊዜ አመልካቾች ማመልከቻቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በሰነድ ዙሪያ ለመወያየት ከHome Energy Assistance ሠራተኞች ጋር በስልክ ወይም በአካል ስብሰባ ያደርጋሉ። ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም የሠራተኛ አባልን ማነጋገር ከፈለጉ ወደ **617-665-6234** ይደውሉ።

ማመልከቻ በፖስታ ከደረሰዎት መመሪያዎቹን ይከተሉ፣ ማመልከቻው ላይ ይፈርሙ እና ከሰነዶችዎ ጋር አያይዘው መልሰው በፖስታ ይላኩልን። 51 Inman St. በሚገኘው ጽሕፈት ቤታችን ማድረስም ይችላሉ። ማመልከቻውን መልሰው ካልላኩ ለHome Energy Assistance ብቁ አይሆኑም።

## ምንም ማሞቂያ የሌለባቸው ድንገተኛ ሁኔታዎች

ማሞቂያ ከሌለዎት፣ የ72 ሰዓት የአገልግሎት መቋረጥ ማሳወቂያ ከደረስዎት ወይም ከነዳጅ ማጠራቀሚያዎ 1/8ኛ የሚያንስ ነዳጅ ካለዎት በተመሳሳይ ቀን እርዳታ ለማግኘት በ**617-665-6234** ይደውሉልን። የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎቶች ለማግኘት የተሟላ እና ብቁ የሆነ ማመልከቻ መዝገብ ውስጥ ሊኖርዎት ይገባል።

## ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች

በተጨማሪም ለሚከተሉት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦

- በጋዝ እና በኤሌክትሪክ ፍጆታ ሒሳቦችዎ ላይ የሚደረጉ ቅናሾች
- የኃይል ቆጣቢነት ማሻሻያዎች
- የHEARTWAP ፕሮግራም (የማሞቂያ ሥርዓትዎን ለመጠገን ወይም ለመተካት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ)

የHome Energy Assistance ሠራተኞች ከእነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር ሊያገናኙዎት ይችላሉ!

ቀጠሮ ለማስያዝ ዛሬውኑ ይደውሉ፦
**617-665-6234**

ኦንላይን ያመልክቱ፦
**www.cambridgema.gov/HeatingHelp**